
# ወደ ቅዱስ ሥልጣኔ




**መግቢያ**

እግዚአብሔር ሲፈጥረን እርሱን እንድናመልከው፥

እርሱ ራሱ አሳወቀን ሥራውን እንድናደንቅ፥

በበለጠ እንድናውቀውና እንድንረዳው፤

ሰው በሰውእነቱ ሲያድግ መልአካዊ መሆን ሲገባው፥
በመሠይጠን ሰይጣናዊ ሲሆን አየነው፤
ሥልጣኔ ለእምነት ማጠናከሪያ መሆን ሲገባው፥
መንፈሳዊ ባሕሬአችንን
በፍቅረ ነዋይና በድሎት ሸፋፈነው፤
ሰበብአዊ ክብራችንን አሳነሰው።

የዚህ ጽሑፍ ዋና አላማ፡-
የሰው ልጅ ቢሠለጥንና ቢሠየጥን[1]
በአንክሮ ለመግለጽ ነው - ያ መጨረሻው እንደማይሆን፥
ካሰብንበትና ካመንበት - አዲስና ቅዱስ ሥልጣኔ እንደሚኖር፥
ከዘመናዊው ሥልጣኔ - ከሥጋዊነታችንም ባሻገር።

## ወደ ቅዱስ ሥልጣኔ

ሥልጣኔ ምኑን ሥልጣኔ ሆነ የሰውን ካላነጻ ልቡናውን፥
የሰውን ካላሻሻለ ጠባዩን - ካላጎላ ጥሩውን፥
ካልቀበረ መጥፎውን፤
ሥልጣኔ ምኑን ሥልጣኔ ሆነ - የሰውን ካላሳደገ ማዕረጉን፥
የሰማዩን ቅዳሴ - በምድር እንድንሰማው ካላስቻለ፥
ሥልጣኔ ምኑን ሥልጣኔ ሆነ -
የሰውን መንፈሳዊ ተቋሙን በሥጋዊነት ካቃለለ፥
ድሃ ሃብታም ሳይል - ሰውን ሁሉ ከመላእክት ጎን ካላስዋለ፤
"ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን...፥"
እያልን እንጸልያለን፤
የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት በምድር ትሆናለች፥

[1] መሠልጠን ወይንስ መሠይጠን የሚለውን ይመልከቱ።
https://ee2463e1-1d4c-42ce-868c-8ee589c5a3cb.filesusr.com/ugd/a268ea_91b830dbd4364937b4374add742f8dd4.pdf

ምድራዊ ትምህርትን እየተማርን፥
ምድራዊ ሥልጣኔንም እያዳበርን?
ከሁሉ አስቀድሞ - እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዲያሰምርልን፥
የእግዚአብሔር ፈቃዱ በምድራችንም እንዲሆን፥
ለሰማያዊ - ቅዱስ ሥልጣኔም እንዲያበቃን፥
የአምላካችን ፈቃዱ በምድራችንም እንዲሆን፥
ማመቻቸት ያሻል ቅድመ ዝግጅቱን።
ከዘመናዊው ሥልጣኔ ባሻገር፥
ሰውን በክብር የሚያስኖር፥
እውነትን እያነገሡ ውሸትን የሚቀብር፥
ፍቅረ ነዋይነትን ወደ ፍቅረ ሰብነት የሚቀይር፥
ግለኛነትን እያጠፋ ማህበራዊ ኑሮን የሚያዳብር፥
ሌላ - ልዩ ጻዲቅ ሥልጣኔ ይኖራል - እኛ ከፈለግን፤
ጥበብን እንሻት - ወደ ሌላ - ልዩ ሥልጣኔ እንሻገር፥
አንድ ብቻ'ማይደል - ያ የጊዜን ሂደት የሚያመላክት ጦር፥
በምድራዊ ሥልጣኔ ብቻ አይታጠርም፥
ያ - እኛነታችንን ይዞ የሚጓዘው ባቡር፤
ይኖራል ሌላ ሥልጣኔ - የታቀደ ለዚች ምድር።
አለው የሰው ልጅ መልካም መንፈስ፥
የሚያጎብዝ - የሚሰጥ ብርቱ ሞራል፥
ስለዚህ - እኛ በአንድነት ካሰብን፥
አናጣም የጋራ ሥልጣኔ ለጋራ ጥቅም የሚውል፥
ወደ ምድራዊነት - ወደ ገንዘብ የማያዘነብል፥
ለሰው ልጅ ለጥሩነቱ ብቻ -
ለሰላም፥ ለፍቅር፥ ለአንድነት የሚውል፥
ሰውን በሥጋውና በመንፈሱ የሚያሻሽል፥
የእድገቱም ሂደትና አቅጣጫ የማያመራ ወደ ሲዖል።

*"እርሱን ብቻ ታሰቡ ዘንድ*

**ለቅዱስ ሥልጣኔ ቅድመ ዝግጅት**

የሥልጣኔአችንን ይዘቱን ብቻ ማወቅ አይበቃም፤
አስቀድሞ በተዘረጋ ሥልጣኔ -
በአንድ መስመር ብቻ መጓዝ አያዋጣም፤
ሥይጣኔ የማይደርስበትን ሥልጣኔ መሻት አይከፋም።
ሁሉን በአዲስ ሥልጣኔ መቀየር ለጊዜው ባይቻልም፥
በዘመኑ የሥልጣኔ ትሩፋቶች እንጠቀም፥
ጥሩ ጥሩውን ብቻ በመቅሰም፥
ጥልቀት ያለውን - መንፈሳዊ ጥበብ በማስቀደም።
*"እንደ እባብ ብልሆች እንደ ርግብም የዋሆች" ማቴ. 10፡2*
በማይክሮስኮፕ የማይታዩ ረቂቃን ጀርሞች - የአስተሳሰብ ተውሳኮች፥
አጋንንት ብንላቸው ሰይጣናት ወይንም ጂኒዎች፥
ብን ብን እያሉ በዙሪያችን፥
ቀዳዳ ሲያገኙ እየገቡ ካይምሮአችን፥
በሳይንሱም ሆነ በሃይማኖት፥
ጥልቅ እያሉ ሳንፈልጋቸው፥
አንዱን እውነት ሺህ እውነት አስመስለው፥
እውነት መሳይ ውሸቶችን ሲሰብኩን
እነርሱ ሊያሟሉ እቅዳቸውን - የማሠይጠን ተግባራቸውን፤
እነርሱ እኛን ከእኛ ሲለያዩን፥
እኛም እኛነታችንን (ተፈጥሮአዊ ማንነታችንን) ረስተን፥
እነርሱኑ መሰልን።

"እባካችሁ - ስለ ፍቅር በስመ አብ ማለት ይቅር"
ይላል ሰይጣን እንዲሉ፥
መጥፎዎች ጥሩ - ጥሩዎችም መጥፎ እስኪመስሉ፥
በሥልጣኔ ውስጥም ኃጢአቶች ይሰበካሉ፤

ኃጢአቶች ሲሰበኩ፥ ሰዎችም በትልቅ በትንሹ ሲጣሉ፥
በዚህ ይታወቃል የሰይጣን ተንኮል ማየሉ።
ወደ ጥፋት የሚያመራ ጎዳና ሲቀየስ፥
ሰውን ወደ ክፋት የሚወስድ ፍልስፍና ሲጠነሰስ፥
እውቀትን - ብልኃትን በመንተራስ፤
ሰይጣን ላመሉ መጽሐፍ ቅዱስ ሲጠቅስ፥
እንደ ባህታዊም ጥሩ አስተማሪ - ጥሩ ሰባኪ እየመሰለ፥
በቀጥተኛው ሃይማኖት ውስጥ አላስፈላጊዎችን እያከለ።

ጥሩ ነገር ከመጥፎው ሲዳቀል፥
ጥሩ ሃሳብ ከመጥፎ ሃሳብ ሲቀላቀል፥
ከአንድ ትውልድ ክፉ ዘመን
ሌላ ትውልድ ክፉ ዘመን ሲከተል፥
ሰው ለሥጋውም ለነፍሱም እንዳይሆን
የአስተሳሰብ ተውሳኮች ከጎናችን፥
ጥሩውን እንዳናይ አይነ ጥላ ሆኑብን።

የዘመኑ ሥልጣኔ - እጅግ ማራኪ፥
ሲያዩት ደስ የሚል ግን መንፈስን አዋኪ፤
እግዚአብሔር አስቀድሞ በፈጠረው አይምሮ
ዘመናዊው እውቀት ተንቆርቁሮ፥
በዚያው ልክ - የሥልጣኔዎች ተውሳክ
ከመሃል እየገባ የሚያውክ፥
ቀና አመለካከቶችን የሚቀጭ፥
ሰባአዊ እድገቶችንም የሚያቀጭጭ።
ሳይንስ ጨካኝ ሆኖ፥
ጨካኝ በሆነ ፍልስፍና ምድሪቱን ለማቃጠል
ከእሳተ ገሞራ የበለጠ ኃይል ተዘጋጅቶ፥
መንፈስ የጎደለው የሥልጣኔ እመርታ፥
መንፈስ የጎደለው ትምህርት በተርታ፥

በስብከት በልመና በምክር የማይገታ
ምድራዊ ሕያዋን ሁሉ አብረው ተያይዘው የሚጠፉበት
የመጨረሻው እልቂት የመጨረሻው ጥፋት
ማሳረጊያው ይኼ ሲሆን፥
በጊዜ ውስጥ ሥልጣኔ የሚያቀርብልን፥
ቁልጭ ብሎ እየታየን እድል ፈንታችን፤...
እንዴት ነው የምንመራው ኑሮአችንን - ካለመሠይጠን?
የሰው ልጅ ሁለት ሆኖ በፍጥረቱ፥
መንፈሳዊነቱን ረስቶ ካደላ ወደ ሥጋዊነቱ፥
ከእሱነቱ ርቆ - መሠይጠኑ አይቀርም፥
ለርሱ የተስማማ ይፈጥራል ልዩ አለም።

ሰው ሥጋዊ ሰው ሆኖ የዘለቀበትን ዘመን እድሜዬ ነው እያለ፤
ፊቱ ሲጨማደድ - የመከፋት ምልክቶችን ሁሉ ከፊቱ እያስተዋለ፥
ለመኖር ሲንገታገት - የሚያጠፋውን ጊዜ ኖርኩበት አለ።
መብረድ እንዳይኖር ማድረግ ያልቻለ፥
በሥልጣኔ ራሱን ከብርድ ተከላከለ፤
ረሃብ እንዳይኖር ማድረግ ያልቻለ፥
በሥልጣኔ ራሱን ከረሃብ ተከላከለ።

ሰው በሥልጣኔ ራሱን መለወጥ ቢችል፥
ተፈጥሮን መቀየር አይችል።
ይዘፍናል፥ ይጨፍራል፥
ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ ያደርጋል፥
ግን ደስታን መፍጠር አይችል፤
ህጻን ልጅ ሲወለድ ያለቅሳል፥
ግን ሲያድግና ሲሸመግል
ከመጣበት ተመልሶ መሄድን - ሞትን ይፈራል።
ሲሞት ይለቀስለታል፥
ግን ሞትን ሰው ራሱ እንደፈጠራት -

የገዛ ሥልጣኔውም ራሱን ማጥፊያ እንደሆነ ይስታል።

የጥንቶቹ  እነ ኖህ፥ አብርሃም፥ ሙሴ፥ ኢያሱ፥
ሳሙኤል፥ ዳዊት፥ ዴቦራ፥ ጌዲዎን፥ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ፥
ጴጥሮስ፥ ጳውሎስ፥ ሐዋርያው ዮሐንስ፥
መንፈሳዊ ሕይወታችንን እየመሩ ቢያቆዩትም፥
ያንን እንደ ሥልጣኔ አልቆጠርነውም።
ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ዘጠኙ ቅዱሳን እና ተከታዮቻቸው ሁሉ፥
እነ ሙሴ ጸሊም፥ ክርስቶስ ሳምራ፥ ወለተ ጴጥሮስ፥
አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ፥ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፥ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፥
ሁሉም በኢትዮጵያውያን መንፈሳውያን በሥራቸው ቢወደሱም፥
ከነርሱ የሚገኘውን መንፈሳዊ ትምህርታቸውን
እንደ ሕይወት መመሪያ አልቆጠርነውም፤
የነርሱ ሥልጣኔ ቅዱስ ሥልጣኔ መሆኑ አልታየንም፥
ሥልጣኔ ማለት ሥጋዊ ምቾትና ድሎትን የሚያመጣ ብቻ መስሎን፥
የመንፈሳዊነታችንን ነገር ረሳን።

ሥይጣኔ እስከ ዛሬ ያልታየ ታላቅ ኃይል መሥርቶ፥
ከከተማ እስከ ገጠር ተንሰራፍቶ፥
ሳይንስን ሲያስተምሩ ሃይማኖትን እንደ ጠላት ቆጥሮ፥
ሰው በነፃ እንዳያስብ በእውቀቶችም ላይ ተጽእኖ አሳደሮ፥
ከኪኒኖች ባሻገር - ጸበልም እንዳይፈውስ ጥርጣሬን ፈጥሮ፥
ታዲያ፡- እንዴት ይታወቅ - ከቁስ አካል የረቀቀ የመንፈስ ነገር፥
በምን አይነት ትምህርት እውነት ይነገር።
ከምናኔ በፊት እውነትን እንዳመጣጡ መቀበልና ማስተናገድ ተስኖን፥
የረቀቀውን የመንፈስን ሥራ እንዳንማርበት
ግማሽ ተፈጥሮአችንን (መንፈሳዊነታችንን) እንዳንኖርበት፥
“ያ አለምን ሸሽተው ገዳም ለሚገቡ ብቻ ነው…” አሉን።
በሳይንስም በሃይማኖትም እውነት እንዳለበት ይገባናል፤
ግን ከሁለቱም የረቀቀውን እንዳናይ ታውረናል።

*“የእግዚአብሔርን እና የኢጋንንትን ጽዋ አንድ አድርጋችሁ*
*መጠጣት አትችሉም” 1ኛ ቆሮ 10፥21*



**<u>አብሮነት - ከተፈጥሮ ጋር ስምም መሆን</u>**

ፍቅር፥ ሰላምና ጤንነት ሁሉም - ለሁሉም፥
ተሳስቦ መኖር - አብሮ መሆን በክፉውም በደጉም፤
    የሰው ልጅ ሁሉ ከዳር እስከ ዳር
    መከፋፈል ሳይኖር - በሃይማኖት በዘር፥
    ሲንቀሳቀስ - ከሚፈልገው ሥፍራ ሲኖር፥
    የወደፊቱ ትውልድ እራሱን የሚያድነው፥
    በተፈጥሮ ማንነቱ እራሱን የሚያቆየው፥
    ማንኛውንም እውቀቱን ለጋራ ጥቅም
    ለፍጡራን ሁሉ - ለሥጋ ብቻ ሳይሆን
    ለመንፈሱም ሲያውለው ነው።

**<u>ለቅዱስ ሥልጣኔ ቅድመ ዝግጅት</u>**

እድል ፈንታችን ሆኖ ሕይወታችን በአጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል፤
በእውነትና በውሸት - በሥጋዊና በመንፈሳዊ አለም
በብርሃንና በጨለማ መካከል ይዋልላል።
ምን እናድርግ - የትኛውን እናንሳ - የትኛውን እንጣል?
ተያይዞ መጥፋት ከሆነ መጨረሻችን፥
ምን አይነት ትምህርት - ምን አይነት እውቀት -
ምን አይነት ሥልጣኔ ነው እኛን ከጥፋት የሚመልሰን?
"ፍሬ በፍሬ ላይ ተደራርቦ ጎተራ ሞላ" እንዲሉ፥
በእውቀቶች ላይ እውቀቶች ተደራርበው በምድራችን ሞሉ።
አዳዲስ እውቀቶችም በአሮጌው ላይ እየተደመሩ፥
እየተቀየሩ - እየተሻሻሉ - የዘመኑን ሥልጣኔዎች አዳበሩ።

> "ፍሬ በፍሬ ላይ ተደራርቦ ጎተራ ይሞላል" ቢባል፥
> "ፍሬ" የተባለውን ከእውቀት ጋር ብናመሳስል፥
> አተርና፥ ማሽላ፥ ጤፍና፥ በቆሎም ጎተራ ይሞላል፥
> ካለ አይነቱ፥ ባህርዩና ጥቅሙ ሲቀላቀል።
> እንግዲህ ጎተራው መሙላቱን ብቻ ከማስተዋል፥
> አልሚና አጥፊውን መለየት ይበልጣል።
> በየትውልዱ ሠላምና ጦርነት ሲፈራረቁ አይተናል፥
> ከጎናችን ሳለ ክፉ መካሪ - ሃይ ሃይ የሚል።

ቀጥታ ከሰው - ወይንም በእጅ አዙር ከዲያቢሎስ
ዛሬም እንዲሁ ከቀድሞው የማይተናነስ፥
በየሥፍራው ሲያጨናንቅ የሥይጣኔ መንፈስ፥
እጅግ ተበራክተው የክፋትና የዘረኝነት ፍሬዎች፥
ጎተራው መሙላቱን ብቻ ከማስተዋል
አልሚና አጥፊውን መለየት ያሻል።

> አዎ! ውሱንነት ጠባዩ የሆነ -
> የምድራዊ ሥልጣኔ ጎተራ ይሞላል፤

ውሱንነት ጠባዩ ስለሆነ - ምድራዊ ሥልጣኔም
መጨረሻ ይኖረዋል።

ከፍሬዎች መካከል ጥሩውን ብቻ የሚቀበል
ልዩ ጎተራ - ልዩ ሥልጣኔ ከወዴት ይፈልቃል?
ለመንፈስም ለሥጋም የሚሆን -
አዲስ ትምህርት (እውቀት) ከወዴት ይገኛል?

ልዩ ትምህርት - ጻዲቅ
ከመንፈሳዊ ተፈጥሮአችን ሳንላቀቅ፥
አዲስ ሥልጣኔ ተፈጥሮን (ጠፈርን) የሚያሳውቅ
ደስ የሚል - ጥሩ ነገር ከተመኘንላት ለዚች ምድር፥
ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለርሷም ብለን ብንኖር፥

እኛ የምናጣውን እርሷ እየሰጠችን፥
ምግብነቷን፥
እኛም እየሰጠናት እርሷም የምታጣውን፥
እንክብካቤዋን፥
እንደዚህ አንዱ ለሌላው እያሰበለት፥
ኑሮን በጋርዮሽ ሲካፈሉት፥
ፍቅር ከነፍሳማው ወደ ግዑዙ
ከግዑዙም ወደ ነፍሳማው ሲዛመት፥
ይህ ነው ባጭሩ ደስታ፥ ሰላምና ጤንነት የምናገኝበት
ምድራዊ ሕይወት።

የማይተነፍሰውን ነፍስ አልባ ብንለው፥
ነፍስ አልባ የምንለውንም ሕይወት እንዳለው የምናውቀው
ተቦጥቡጦ ሲያልቅ - ከመኖር ወዳለመኖር ሲሸጋገር ነው።
የጸሐይ ሙቀት፥ የውሃ፥ የአየርና የአፈር ሕይወት ሰጪነት፥
አንድ አይነት ስለሆነ ለእንስሳት እንዲሁም ለእጽዋት፥
ሁሉም አብሮ ሲሰምር ነውና የሚራዘም ሕይወት፥
ካለ መቃወስ - ካለ መዛባት፤

አንዱ ከሌላው ሳይለይ ነውና ምድራዊ ሕይወትም የሚቀጥል፥
በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ተፈጥሮአዊ ሂደት እንዳይጓደል፥
እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ልዩ ክብር ሰጠው፥
ለምድሪቱም አስተዳዳሪ አድርጎ ሾመው፤
ታዲያ ምንድነው የሰው ልጅ ግዴታ - ከኛ የሚጠበቀው?
የነፍሳማውንም የነፍስ አልባውንም ሥራ
እንደ ተፈጥሮአዊ ተግዳሮት ብንቆጥረው፥
ምንድነው ያ ሥራ - ለሁላችንም የሚስማማ?
ሁላችንንም በጋራ የሚያስኖር - ሁላችንንም የሚያስማማ።
ኑሮን በአብሮነት እና በአንድነት ለመምራት፥
ለሰው ልጅ ተሰጥቶታል መንፈሳዊ - ሕሊናዊ ብቃት፥
ፍቅር፥ ሰላም፥ ጤንነትና ደስታን ለራስ ሳይሆን፥
ለሌላው እየሰጡ ማግኘት፤
ይህ ነው ከሰው የሚጠበቅ ተፈጥሮአዊ ተግዳሮት
ለአዲስና ለቅዱስ ሥልጣኔ የሚሆን ቅድመ ዝግጅት።
*“ደስ ከሚለው ጋር ደስ ይበላችሁ፤ ከሚያለቅሰውም ጋር አልቅሱ።” ሮሜ 12፡ 15*

**መሠልጠን ካለ መሠይጠን**

ሰማይ አንድ ብቻ - ምድርም አንድ ብቻ
ሥልጣኔም አንድ ብቻ አይደለም፤
አደገኛ ሥልጣኔ ይኖራል - ከዚህም ከዚያም አለም፥
በሳይንሱም በሃይማኖት ውስጥም እየገባ ነገር የሚያጣምም።
እውነት ግን አንድ አንጂ - ሁለት - ሦስት አይሆንም፤
ስለዚህ ካሰብንበት ሁላችንም፥
አዲስ ትምህርት - አዲስ ጥበብ አይታጣም፥
ከአንድ እውነት የሚመነጭ - በሳይንስም በሃይማኖትም።
ጸሎታችንን እየሰማ - እግዚአብሔር ዝም አይልም፤
ሥይጣኔ ሲነግሥብን አይተወንም።

የዘመኑ ሥልጣኔ የወጣ ከአንድ በር፥
ከሰማኒያ አንዱ በሮች - ሄኖክ ከሚሉት መንደር፤
ማን ያውቃል ከተቀሩት ሰማኒያ በሮች መካከል፥
አንዱ በተረኛነት ለኛ መከፈቱን ቢቀጥል።
ልዩና አዲስ ሥልጣኔ ከሰማይ ወደ ምድራችን ቢሰማራ፥
ወገግ ፈካ ብሎ ደስታን ፍንጥቅ እንደ ፀሐይ ጮራ፥
ረሃብ፥ ጭንቀት፥ ሃዘን፥ በሽታን ሊያጠፋ፥
ጨለማ ምድራችንን ሊያበራ፤
አለን ተስፋ - ቅዱስ ሥልጣኔ ይሰጣል ለሰው።
በአንድ እግሩ ቢቆም ተክለ ሃይማኖት፥
ለምን ይጨነቅ ለእግሩ ሕመም - ምን ገዶት፥
ምን ገዶት ይጨነቅ
ከምድር ሄዶ መጥቆ ወደ ቂርያተ መላእክት፥
ደስ እያለው እየተመሰጠ በጸሎት፥
ሰባት ዓመታት እንደ አንድ ሰዓት።
አይ! ይህንን ቢመስል አዲሱ ሥልጣኔ
እንደ ተክልዬ፥
የሚገኝ ቢሆን ገዳም በመግባት - በምናኔ፥
ወይንም ከከተማ - በየትምህርት ቤቱ የሚሰጥ፥
የማያስመንን - ከምድራችን የማያስርቅ፥
ልዩ እውቀት - ብዙም የማያራቅቅ፥
ከእስላሞችም ቢሆን ከአይሁዶች፥
ከሂንዱ፥ ከቡድሃም ቢሆን ከሌሎች፥
ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራእይ ባንድ ዓመት፥
ከሌሎችም መጻሕፍት በጥቂት፥
ግን ከሁሉም መንፈሳዊ ጥንካሬና ብርታት፥
በአንድ እግዚአብሔር በአንድ እውነት፥
ታዲያ ምናለበት ሳይንስ ቢደባለቅበት፥

ያም እውነት ከሆነ፥
የእግዚአብሔርን ሥራ የምናደንቅበት፥
*“እግዚአብሔርን በተቀደሱ ቦታዎች አመስግኑት፥*
*በኀይሉ ጽናት አመስግኑት….መዝ. 150፥1*
የምንልበት።

***<u>መንፈሳዊ ሥልጣኔ</u>***
የዘመኑ ሥልጣኔ ምድራዊ ከሆነ - ሥጋዊ፥
ቅዱስ ሥልጣኔ መኖር አለበት - ምድራዊ ያልሆነ - ሰማያዊ
በውስጡ ክፉትና መጥፎ ነገር የሌለው፥
የሰብእናችንን ደረጃ ከፍ ከፍ የሚያደርገው።
መቼም የእግዚአብሔር ፈቃድህ ከምድራችንም መዳረሱ አይቀር፥
የገንዘብ አይኑ ሲታወር፥
ውሸት በእውነት ሲቀየር፥
በአህጉራት መካከል የፖተሊካ ድንበር ሲቀር፥
ጦር በመስበቅ ፋንታ - አምራች ሲሆን ወታደር፥
የዛን ጊዜ፡-
በመንፈስ አርቅቀው የሚሄዱ ፈላስፎች - የዋህነትን የሚሰርጹ እርግቦች
የረቀቁ ሃሳቦችን ያፈልቃሉ፥
መንፈሳዊ ሥልጣኔንም ካለ ገደብ ያሳድጋሉ።
አንድ እውቀትን ከእውነት ጋር በማዛመድ
አለም አቀፍ መንፈሳዊ እውቀትን
ከአለም አቀፍ እውነቶች ጋር በማጣመር፥
የአንድ ሃይማኖት - የአንድ አለም አቀፍ ሃይማኖት ነገር፥
እውነታው ይህ ቢሆን - ከምድር ወደ ሰማይ የሚያሻግር፥
እጹብ ድንቅ የሚባል -
ብዙ ሥራዎች መሥራትን የሚያስችል ካለ ችግር፥
ከአዳም ኃጢአት የጀመረ - ትግል ፍትጊያ ከስበት (gravity) ጋር፥

ምድራዊ ሥራ - ትግል ፍትጊያን የሚያስቀር፥
መንፈሳዊ ጥንካሬ - ሥጋዊ ድካምን የሚያስቀር፥
እንዲህና ይህንን ይመስላል - በመንፈስ አርቅቆ መሻገር፥
ሥጋን ቁጭ አድርጎ
መንፈሳዊ ማንነትን ይዞ መንሸራሸር።
በቅሎ - ፈረስ ከማስቸገር፥
መኪና - አይሮፕላን ከመሳፈር፥
ካለ አካላዊ ንኪኪ እዚህም እዚያም መገኘት
ሙሉ አካላዊ ጤንነት፥
ራስ ምታትና ትኩሳት የማያገኘው፥
የመንፈስ መረበሽ - የአይምሮ ጭንቀት የሌለበት፥
ፍቅርና ደስታ - ከዚህም ከዚያም ቤት።
ይህንን - ሌላም - ሌላም ቢሆን የእኛ ምኞት፥
በቅዱስ ሥልጣኔ የሚገኝ ትሩፋት፥
የእኛ ብለን - የእኛ ከሆነው -
ከድቁናም ቢሆን ከመድረሳ፤
መንፈሳዊነትን ለማሳደግ ብንነሳ፥
አየር ምድሪቱን የከበበውን ያህል፥
እውነት በያለበት ሲበተን
ከክርስቲያንም ቢሆን ከእስላም፥
ከሂንዱም ቢሆን ከቡድሃ፥
ከአራቱም ማዕዘን እውነትን የፈለጋት ያገኛታል።
*"በአንድ መንፈስና በሰላም ማሰሪያነት እየተጠበቃችሁ..." ኤፌ. 4፡3*
ያቺን ሁለንተናዊ እውነት የጋራ በማድረግ
የሰብእነታችንን መንፈሳዊ ባህርይ በማሳደግ፥
ይህ ቢሆን የጋራ ትምህርት ሁሉም የሚማረው፥
ሁላችን ተስማምተን መሠረታዊ እውቀት የምናደርገው፥
ከባድ ቢመስልም ይቻላል፤

የምንመኘው ቅዱስ ምኞት ሁሉ በቅዱስ ሥልጣኔ ይገኛል።

*"እርስ በርሳችሁ በአንድ ሃሳብ ተስማሙ.." ሮሜ 12፥16*

*"የሁሉም ፍጻሜ የባልንጀራችሁን መከራ እየተቀበላችሁ*
*አንድ ልብ ትሆኑ ዘንድ ነው...." 1ኛ ጴጥ. 3፥8*

## <u>*መደምደሚያ*</u>

ምድራዊ ሥልጣኔ ለምድር ስለሆነ ግልጋሎቱ፥
ምድራዊ እውቀትም ምድራዊ ነውና መሠረቱ፥
ይዞን ጭልጥ አለ ሰማያዊ ተፈጥሮአችንን ይዞ፥
እኛንም ለወጠን አፍዝዞ አደንዝዞ።
አንዱን ጎናችንን - ሰማያዊነታችንን ረስተን፥
ያልሆነውን መሆናችን እራሳችንን እንደጎዳን፥
ብዙ ቆይቶም ቢሆን ውስጣዊ መንፈሳችን ቀሰቀሰን፤
የምድራዊ ኑሮአችን ድቀት አነቃቃን።

ጠፍተን አንጠፋም - ብሩህ ተስፋ ይታየናል፥
በቅዱስ መንፈስ - ቅዱስ ሥልጣኔ ነፃ ያወጣናል።

ከምድራዊ ሥልጣኔ ጋር መንፈሳዊነትን አክሎ፥
ክፋት ምቀኝነትን ደምስሶ - ጦርነትን በሰላም ተክቶ፥
ድሎትና ምቾትን በመጠኑ አስተካክሎ፥
ፍቅር ደስታን አጎናጽፎ፥
አዲስ ሥልጣኔ አይቀርም ይመጣል፥
ስንፈልገው ይገኛል - ምኞታችን ያ ቢሆን።

አሮጌው ሥልጣኔ ሰውን ወደ ክፋት የሚመራው፥
ተለውጦ አዲስ ሆኖ ሰውን ወደ ጥሩነት እንዲመራው፥
በሃሳብና በምናብ የምንገነባው - ተግባራዊም የምናደርገው፥
በእግዚአብሔር ቸርነት ቀስ በቀስ የምናሳድገው፥
አሁን ነው - የአዲስና የቅዱስ ሥልጣኔ ጊዜው።

ቅዱስ ሥልጣኔ ከቅዱስ ሥራ ይጀምራል፥
ቅዱሱም ከሰማይ ይመጣል፤
አሮጌው በአዲሱ ይተካል፤
እስከዛሬ ለወደፊትም የምንጸልያት ጸሎታችን ትሰማለች፥
የእግዚአብሔርም ፈቃድ በሰማይ እንደሆነች፥
እንዲሁም በምድርም ትሆናለች።

አብሮ በመሆን ሁሉም ስለሚቻል፥
እምነትና እውነትን ይዘን በመቆየታችን፥
በመንፈሳዊነታችን አርቅቀን ስንሄድ ከምድራዊነታችን ተላቀን፥
በአዲስና በቅዱስ ሥልጣኔ እንደገና ያብባል ሕይወታችን።